# የቸገረው እርጉዝ ያገባል

## ትዕይንት አንድ

1. / አንድ ከመንገድ ዳር ካለ የመኪና ማጠቢያ ቦታ/

1.1 ከመኪና ማጠቢያው ውስጥ የተለያዩ መኪናዎች በወጣትነት እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ወጣቶች መኪናዎችን በማጠብ ላይ ተሰማርተው ይታያሉ::

ማትያስ - ከመኪና ማጠቢያው መግቢያው ላይ ከሌሎች መኪኖች ፊት ለዋናው መንገድ የቀረበችውን መኪና በባልዲ የያዘውን ውሃ እየቸለሰበት ሲያጥብ በቅርበት ይታያል::

1.2 ከሚኪና ማጠቢያው በአንደኛው በኩል ካለው የእግረኞች መንገድ ላይ

1.2.1 አቶ ታምሩና ባለቤታቸው ወ/ሮ ስንዱ ጎን ለጎን ሆነው ተረጋግተው እያወሩ ወደ መኪና ማቆሚያው ሲመጡ ይታያሉ::

ታምሩ - ከመኪናው ማጠቢያ አካባቢ እንደ ደረሱ ልጃቸውን ማትያስን ሲመለከቱ ከፍተኛ ደንግጠው እየቆሙና እሱ ነው አይደለም በሚል ዓይኖቻቸውን እየጠራረጉ አፍጥጠው ይቀራሉ::

ማትያስ - የወላጆቹን መምጣት ሳይመለከት አጠባውን ቀጥሎ ይታያል

ስንዱ - መራመዳቸውን ቀጥለው መለስ ብለው ሲያዩ ባለቤታቸውን ከአጠገባቸው አለመኖር ሲመለከቱ ደንገጥ ብለው ይቆሙና መለስ ብለው ወደ መጡበት ሲመለከቱ ወደ ኋላ የቀሩት ባለቤታቸው በቆሙበት ደርቀው ሲመለከቷቸው ድንጋጤአቸው እየበረታ ወደ ባለቤታቸው ይመለሳሉ::

ታምሩ - በድንጋጤ ደርቀው ከቀቆሙበት ቦታ ከልጃቸው ከማትያስ ላይ እንዳፈጠጡ ፊታቸው ከርቀት እየቀረበ ይታያል::

# ትዕይንት ሁለት

## ምልሰት

2. ከአንድ የዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምረቃ በዓል ላይ

2.1 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የምረቃ በዓል ከሚካሄድበት አዳራሽ ውስጥ ያሉትና ካባቸውን የለበሱ ተማሪዎች በብዛት እየታዩ መለዮአቸውን አውልቀው ወደ ጣሪያው እየወረወሩና በደስታ እየፈነጠዙ ይታያሉ::

2.1.1 ተማሪዎቹ እየታዩ የደስታ ጭብጨባ፥ እልልታና ፉጨት ይሰማል

# ትዕይንት ሦስት

## ከምልሰት መልስ

ታምሩ - ከላይ በድንጋጤ ደርቀው ከቆሙበት ቦታ ፊታቸው ከቅርበት እየራቀ መታየት እንደ ጀመረ ...

ስንዱ - ከአጠገባቸው ደርሰው እየቆሙ ባለቤታቸውን በአንድ እጃቸው ይነቀንቋቸዋል

ታምሩ - በድንጋጤ ከሃሳባቸው በመባነን ዓይኖቻቸውን ከልጃቸው ላይ በመንቀል ወደ ባለቤታቸው ዞረው ያያሉ::

ስንዱ - ደንግጠው ግራ በመጋባት እያዩአቸው ምን ሆኑ?

ታምሩ - እንዳይደንግጡ ምንም ሳይናገሩ የቀኝ እጃቸውን በመዘርጋት የሌባ ጣታቸውን በመቀሰር ወደ ማትያስ ያመለክታሉ ::

ስንዱ - ወደ ማትያስ ዞረው ይመለከታሉ

ማትያስ - በወላጆቹ አመለካከት ወደ እነሱ ሳያይ ከሥራው ላይ እንዳተኮረ ይታያል

ስንዱ - ክፉኛ ደንግጠው በሁለት እጆቻቸው እራሳቸውን ይዘው ከማትያስ ላይ እንዳፈጠጡ ውይ!!!

ማትያስ - መኪናውን እያጠበ ድንገት መለስ ሲል ወላጆቹን ይመለከትና ክፉኛ ደንግጦ የያዘውን ማጠቢያ እየጣለ ቀና ብሎ ሲመለከታቸው ፊቱ ከርቀት እየቀረበ ይታያል::

# ትዕይንት አራት

4. በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኘው ከአቶ ታምሩ ሳሎን

4.1 ሳሎኑ በአንድ ጎኑ እንደ መኝታ ቤትም የሚያገለግል በመሆኑ የሶፋ ወንበሮች እና የተነጠፈ አልጋ እንዲሁም አሮጌ የእቃ ማስቀመጫ ኮሞዲኖ ይገኛል።

4.1.1 ከላይኛው ትዕይንት መጨረሻ ላይ በቅርበት ይታይ የነበረውን የማትያስን ፊት በመታከክ ወይም በመደባለቅ አሁንም በሳሎኑ ውስጥ ካለው ኮሞዲኖ ላይ በፍሬም ውስጥ የተቀመጠውና በዲግሪ የተመረቀበትን የማትያስን ፎቶግራፍ ከቅርበት መታየት ጀምሮ የወ/ሮ ስንዱ ለቅሶ መሰማት ሲጀምር ፎቶግራፉ እየራቀ ከሶፋው ወንበር ላይ የተቀመጡት ማትያስና ወላጆቹ መታየት ይጀምራሉ።

4.1.2 ስንዱ እያለቀሱ፥ ታምሩ ደግሞ ዓይኖቻቸውን ከአንድ ቦታ ላይ ተክለው አንገታቸውን በቁጭት እየነቀነቁ ሲቆዝሙና ... ማትያስ በመጨነቅ ሲወራጩ ይታያሉ።

ስንዱ - እያነቡ እ. ሀ. ሀ ... አዎን ... እድሌ ነው ለዚህ ያበቃኝ ... እ. ሀ. ሀ

ማትያስ - ኧረ በፈጠረሽ እማዬ ...ምንድን ነው ይህን ያህል መማረር...

ታምሩ - መለስ ብለው በትዝብትና በቁጭት እያፈጠጡበት - ተው እ. ን. ጂ!

ተው እንጂ ልጄ። አዎን እኛ እኮ ስማ... አለመማራችን ያተረፈልን ድህነት - ላንተም ለልጃችን ከምናወርስህ ተምረህ ሰው ትሆናለህ፥ ተከብረህ ታስከብረናለህ ብለን ነበር። የሌለንን ገንዘብ እየገፈገፍን አንተ ግን - አንተ ግን

ማትያስ - አቋርጧቸው በፈሪ ልሳን - እ. ኔ እኔም ብሆን አባዬ ...

ታምሩ - አቋርጠውት በንዴት እየተመናጨቁ - አባዬህን ተወኝ ስልህ!! አሰዳቢ ሁላ!!

ማትያስ - ለምን ... ለምን እኔንስ አታዳምጠኝም

ስንዱ - እንባ እየቀደማቸው - የምትሠራውን ሥራ እያየነው

... አዎን ... አንተ ባታውቀውና ባይገባህ ነው እንጂ ... አንተ ዛሬ የምታጥበውን

የሰው መኪና ዛሬ ጓደኞችህ ገዝተውት እያሽከረከሩትና እየነዱት በአጠገባችን

ሽው ብለው እያፏጩብን ሲሄዱ ነው የምናየው::

ታምሩ - እኮ አንተ ግን ይሄውና ተምሮ እንዳልተማረ ሰው ተሽቆለከልክና የደንቆሮዎቹ

ሥራ ሻጠቀህ የሰውን ቆርቆሮ ትፈትጋለህ::

ማትያስ - በምጸት ፈገግ እያለ - በተማርኩበት ሙያ ሥራ ፈልጌ እስከማገኝ ድረስ ቁጭ

ከምል ብዬ በሠራሁት ሥራ ነው ይ. ሄ. ሁሉ ውርጅብኝ?!

ታምሩ - አለ ደረጃህ ? ካለ ቦታህ ወርደህና ተዋርደህ ስታበቃም አደል እንዴ ... እኛን

ጭምር ያዋረድከን !!!

ማትያስ - እንባ እያነቀው - ካለ ቦታዬ ስለ መሆኑ አውቃለሁ ... ግን ... ግን አባዬ ...

እናንተ ስትማሩ እኔ ለማስተማር ያወጣችሁትን ወጭም ሆነ የደከማችሁትን

ድካም ሁሉ ስለማውቀው እናንተን ለመርዳት በተማርኩት ሙያ ሥራ ለማግኘ

በሚል ፈልጌና አስፈልጌ ማግኘቱ ቢቸግረኝ ... ዛሬም እናንተን ከማስቸገር ...

ባንድ ፊት “ እስኪያልፍ ያለፋል” እንደሚሉት የራሴን ጥቃቅን ወጭዎች

ቢሸፍንልኝ ብዬ ሲሆን በላላ ጎን ...

ታምሩ - አቋርጠውት- እኮ እኛ እምንበላውን በልተህ ከማደር መዋረድን መርጠህ አይደል?

ማትያስ - ስለ ሆዴ ማሰብ ብቻ ሳይሆን አባዬ እንዲያው መናገር የማልፈልገውን እንድናገር

ፈልገህ ከሆነ / እልህና እንባ እየተናነቀውና ወደ እናቱ እንደ መጠቆም እያየ /

እ. ማ - እማዬ የታመመች ጊዜ

ታምሩ - አቋርጠውት በድንጋጤ - እ . የ . ታመመች ጊዜ

ማትያስ - እናስ ... ሆስፒታል ገብታ መተኛት አለባት የተባለች ጊዜ እንኳንስ ለሆስፒታል

የምትከፍለው ይቅርና ለመድኃኒት መግዣም የሚሆን ቸገረኝ ብለህ ከዚህ ከደጃፋችን

ካለው ከድንጋይ ላይ ቁጭ ብለህ እንደ ሴት ያለቀስክበትን ጊዜ እረሳኸው!!!

ስንዱ - በተቀመጡበት በድንጋጤ ደንዝዘው ይቀራሉ

ታምሩ - እንባ እያነቃቸው እ. ና .. የዛን የዛን ጊዜ ሥራ ገባሁ ብለህ የምትሰጠኝ ገንዘብ ...

ማትያስ - አዎን - አዎን አባባ ... የእናቴን ሕይወት ለማትረፍ ... መኪኖችን አይደለም

የሰዎችንም እግር ቢሆን ከማጠብ አልመለስም ነ. በ. ረ. ና

ታምሩ - አቋርጠውት - እኮ “ የቸገረው እርጉዝ ያገባል” እሚባለው ተረት ይሄው አይደል

ከተቀመጡበት እየተነሱ - ማረን ማረን የኔ ልጅ

ማትያስ - ከተቀመጠበት ተፈናጥሮ እየተነሳ - ኧ- ረ አባዬ

/ መሸጋገሪያ ሙዚቃ ይገባል/